# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር

## የተሽከርካሪዎች የመለያ ቁጥር ሠሌዳ ዓይነቶችና ምልክቶች መወሰኛ እና የአገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 1050/2017

# Federal Democratic Republic of Ethiopia

# Ministry of Transport and Logistics

## Types of Vehicles Identification Number Plate and Symbols Determination and Service Delivery Directive No. 1050/2025

መጋቢት 2017 ዓ.ም
አዲስ አበባ

## መመሪያ ቁጥር 1050/2017

## የተሽከርካሪዎች የመለያ ቁጥር ሠሌዳ ዓይነቶችና ምልክቶች መወሰኛ እና የአገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ

ቀደም ሲል የነበረው የተሽከርካሪ መለያ ቁጥር ሠሌዳ አመራረት እና አሰረጫጨት የአሠራር ክፍተት የነበረበትና የሀብት ብክነት ሲስተዋልበት የቆየ በመሆኑ ይህን የሀብት ብክነት በማስቀረት በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የሚመጣውን የሠሌዳ ጥሬ ዕቃ በአግባቡ በመጠቀም የመንግሥትን ሀብት ከብክነት ለመታደግ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በተለያዩ ምክንያቶች ተመላሽ የሚደረጉ የተሽከርካሪ መለያ ቁጥር ሠሌዳዎች አወጋገድን በተመለከተ ካሁን በፊት የተዘረጋ ሥርዓት ባለመኖሩና በሕግ ማዕቀፍ በማካተትና በሥርዓት እንዲመራ ማድረግ በማስፈለጉ፤

ካሁን በፊት በነበረው አሠራር የዕለት፣ የተላላፊ እና የቋሚ መለያ ቁጥር ሠሌዳ አገልግሎት አሰጣጥ ለፎርጅድ፣ ለብልሹ አሠራርና ለበርካታ ወንጀሎች የተጋለጠ በመሆኑ ይህንን አሠራር ማሻሻልና የተሽከርካሪ መለያ ቁጥር ሠሌዳን የምርት፣

## Directive No. 1050/2025

## Types of Vehicles Identification Number Plate and Symbols Determination and Service Delivery Directive

**Whereas**, the previous system of manufacturing and distribution of vehicles identification number plate had a gap and wastage of wealth, by avoiding this wastage of wealth and by using proper row materials that are imported with high foriegn currency, it is necessary to put in place a system which enables to save public wealth;

**Whereas,** there was no system enabling to discrd the vehicles identification plate returned back due to different reasons and it is necessary to include in legal fram work and impliement it;

**Whereas,** in the previous existing service providing system of temporary, transfrable and permanent identification number plate was exposed to forgery, corruption and many crimes, it is necessary to improve this system and to modernize the system of manufacturing, distribution and discarding of vehicles identification number plate through

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport and Logistics

የስርጭትና የአወጋገድ ሥርዓቱን በማዘመንና በቴክኖሎጂ በመታገዝ ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ በማስፈለጉ፤

የተሽከርካሪዎችን መለያ ቁጥር ሠሌዳ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን መሠረት ያደረገ እንዲሆን በማድረግ፣ ካሁን በፊት የነበረውን አሠራር በመለወጥ እስካሁን በሀገሪቱ ውስጥ የተመዘገቡ ተሽከርካሪዎች የመለያ ቁጥር ሠሌዳ ለውጥ አድርገው እንደ አዲስ የሚመዘገቡበትንና ወደ ፊት የሚመዘገቡትም በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥ የሆነና ተከታታይነት ያለው የመለያ ቁጥር ሠሌዳ እንዲኖራቸው ማድረግ ሀገራዊ ፋይዳው የጎላ በመሆኑ፤

የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር በመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 1274/2014 አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ **“የተሽከርካሪዎች የመለያ ቁጥር ሠሌዳ ዓይነቶችና ምልክቶች መወሰኛ እና የአገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር** 1050/2017” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

technological support and strict follow up and control;

**Whereas,** it has become necessary to cnform with international agreements the vehicles identification number plate by altering the previous operation and to make change of identification number plate and to be registered again vehicles that was registered and to having uniform and consecutive identification number plate vehicles that will be registered;

Now, therefore, his Directive is issued by the Ministry of Transport and Logistics in accordance with Article 12 sub article (2) of Road Transport Proclamation No.1274/2022.

## Part One

## General Provisions

### 1. Short Title

This Directive may be cited as the " **Types of Vehicles Identification Number Plate and Symbols Determination and Service Delivery Directive No. 1050/2025.**"

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) **"የተሽከርካሪ አምራች''** ማለት ተሽከርካሪዎችን በሀገር ውስጥ የሚያመርት ድርጅት ነው፡፡

2) **"የተሽከርካሪ ገጣጣሚ ድርጅት"** ማለት በሀገር ውስጥ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የተሽከርካሪን አካላት በማምረት ወይም በማስመጣት የሚገጣጥም ሰው ነው፡፡

3) **"የተሽከርካሪ አስመጪ''** ማለት ማንኛውም ያገለገሉ ወይም አዲስ ከውጭ ሀገር ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት ተሽከርካሪውን በመግዛትና በመሸጥ በንግድ ስራ ላይ የተሰማራ ሰው ነው፡፡

4) **"የጉምሩክ ጣቢያ"** ማለት ተሽከርካሪዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንደገቡ በሽያጭ ከመተላለፋቸው በፊት አስፈላጊዉ የመንግሥት ቀረጥ የሚሰበሰብበት ቦታ ነው፡፡

5) **"የመለያ ቁጥር ሠሌዳ ማምረት"** ማለት በመላው ሀገሪቱ ለሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች በማዕከል ደረጃ የመለያ ቁጥር ሠሌዳን እንዲታተም ማድረግ ነው፡፡

6) **"የመለያ ቁጥር ሠሌዳ ስርጭት"** ማለት

## 2. Definitions

In this Directive, unless the context requires otherwise, words shall have the following meanings:

1) **"Vehicles manufacturer"** means an Enterprise engaged in the business of manufacturing vehicles within the country.

2) **"Vehicles Assembler Enterprise"** means an enterprise engaged in the business of assembling vehicles within the country by manufacturing or importing spare parts of vehicles in whole or in part.

3) **"Vehicles Importer"** means any person who imports used or new vehicles and engaged in the business of buying and selling vehicles.

4) **"Customs Station"** means the place designated to collection of duties when vehicles imported and before transfer by sale.

5) **"Manufacturing of Identification number plate"** means producing identification number plates in central level to all vehicles moving all over the country.

6) **"Distribution of Identification number plate"** means giving produced

የታተሙትን የመለያ ቁጥር ሠሌዳዎችን ለአስመጭዎች፣ ለገጣጣሚዎች፣ ለአምራቾች ወይም ለግለሰቦች መስጠት ነው፡፡

7) **“የመለያ ቁጥር ሠሌዳን መለጠፍ”** ማለት ከውጭ ሀገር ለገባ ወይም በሀገር ውስጥ ለተመረተ ወይም ለተገጣጠመ ተሽከርካሪ የተፈቀደለትን የመለያ ቁጥር ሠሌዳ በተሽከርካሪው ላይ ማሰር ነው፡፡

8) **“የመለያ ቁጥር ሠሌዳን ማስወገድ”** ማለት የመለያ ቁጥር ሠሌዳ ለውጥ በሚደረግበት ጊዜ ተመላሽ የሆነውን መለያ ቁጥር ሠሌዳ በመቆራረጥ ወይም በማቅለጥ ማስወገድ ነው፡፡

9) **“በኤሌክትሪክ ወይም በታዳሽ ኃይል የሚሠራ ተሽከርካሪ”** ማለት የነዳጅ ኃይልን ሳይጠቀም ወይም ከነዳጅ ውጭ በሆነ ኃይል የሚሠራ ተሽከርካሪ ነው፡፡

10) **“የአካል ጉዳተኛ ተሽከርካሪ”** ማለት ለአካል ጉዳተኞች ብቻ የተፈቀደና ከሌሎች ተሽከርካሪዎች የሚለይበት ልዩ ምልክት የሚደረግበት ተሽከርካሪ ነው፡፡

11) **‘‘ሰው’’** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

12) በመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 1274/2014 እና በተሽከርካሪ መለያ፣ መመርመሪያና መመዝገቢያ አዋጅ ቁጥር

identification number plates to importers, assemblers, manufacturer or individuals.

7) **“Affixing of Identification number plate”** means bonding authorised identification number plate on imported or manufactured or assembled vehicle within the country.

8) **“Discarding of Identification number plate”** means removal of retuned identification number plate by cutting up or smelting when change of identification number plate taken place.

9) **“Vehicle Used Electric or Renewable Energy”** means a vehicle working without fuel energy or working with energy out of fuel energy.

10) **“Vehicle of Handicap persons”** means a vehicle designated and used solely for the transport of physically disabled persons and affixing special sign distinguishing from other vehicles.

11) **“Person”** means any natural or juridical person.

12) Definitions given under Road Transport Proclamation No.1274/ 2022 and Vehicles Identification,

681/2002 ላይ ትርጉም የተሰጣቸው ቃላትና ሐረጎች እንደ አግባብነታቸው ለዚህ መመሪያም ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

13) ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

## 3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በመላው ሀገሪቱ በተመዘገቡና ለምዝገባ በሚቀርቡ ተሽከርካሪዎች፣ በተሽከርካሪ መዝጋቢ አካላት፣ በተሽከርካሪ አምራቾች፣ አስመጪዎች፤ ገጣጣሚ ድርጅቶች፤ በኢትዮጵያ በሚገኙ ዓለም አቀፍ እና አህጉር አቀፍ ተቋማት፣ እንዲሁም ግለሰቦች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 4. <u>የመመሪያው ዓላማዎች</u>

መመሪያው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1) የተሽከርካሪዎችን መለያ ቁጥር ሠሌዳ ዓይነቶችና ምልክቶችን ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን መሠረት ያደረጉ እንዲሆኑ ማድረግ፤
2) በሀገር አቀፍ ደረጃ የመለያ ቁጥር ሠሌዳ አገልግሎት በይዘት፣ በዓይነት እና በመጠን ወጥ እንዲሆን ማድረግ፤
3) የመለያ ቁጥር ሠሌዳ ምርት፣ ስርጭት፣ አወጋገድ፣ የተሽከርካሪዎችን የመረጃ አያያዝ እና ቁጥጥር በቴክኖሎጂ የተደገፈ እንዲሆን ማድረግ፤

ነው፡፡

Inspection and Registration Proclamation No.681/2010 shall be applicable to this directive where appropriate.

13) Provisions of this Directive set out in the masculine gender shall also apply to the feminine gender.

## 3. <u>Scope of Application</u>

This Directive shall be applicable to vehcles registered and to be registered all over the country, vehicles registrars, vehicles manufacturers, importers, assembler enterprises, international and continental institutions and individuals living in Ethiopia.

## 4. <u>Objectives</u>

The Directive has the following objectives:

1) To make kinds of vehicles identification number plate and signs international agreements baseline;
2) To make service of identification number plate uniform at national level in content, kind and size;
3) To support with technology information of manufacturing, distribution and discarding of identification number plate and vehicles handling information and supervision.

# ክፍል ሁለት

## ስለ ተሽከርካሪ መለያ ቁጥር ሠሌዳ አገልግሎት አሰጣጥ

5. **ስለ ተሽከርካሪ መለያ ቁጥር ሠሌዳ ዓይነቶችና ምልክቶች**

1) የተሽከርካሪ መለያ ቁጥር ሠሌዳ ዓይነቶች እና ምልክቶች ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ "ሀ" መሠረት ይሆናል፡፡
2) ሚኒስቴሩ የተሽከርካሪ መለያ ቁጥር ሠሌዳን በሀገር አቀፍ ደረጃ እንዲመረት ማድረግና ማሰራጨት አለበት፡፡
3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደ ተጠበቀ ሆኖ በሀገሪቱ የሚመዘገቡ ሁሉም ተሽከርካሪዎች የሚለጥፉት የመለያ ቁጥር ሠሌዳ ላይ የኢትዮጵያ ካርታ እና ሀገራችን ባጸደቀችው ዓለም አቀፍ ስምምነት መሠረት የተሰጣትን ሀገራዊ ልዩ ምልክት "ETH"፣ እንዲሁም "ኢት" የሚል የግእዝ ፊደላት እና የላቲን ፊደላት ይዞት እንዲኖረው ይደረጋል፡፡
4) ሚኒስቴሩ የመለያ ቁጥር ሠሌዳ አሰጣጡ ሦስት የላቲን ፊደላትን እና አራት ቁጥሮችን በመጠቀም ተከታታይ ቁጥር ያላቸው የመለያ ቁጥር ሠሌዳዎችን እንዲመረቱ ያደርጋል፡፡

# Part Two

## Service Delivery of Vehicles Identification Number Plates

5. **Types of Vehicles Identification Number Plates and signs**

1) Types of Vehicles Identification Number Plates and symbols shall be in accordance with Schedule "A" attached to this Directive.
2) The Ministry shall produce and distribute vehicles identification number plates at national level.
3) Without prejudice to the provisions of sub-article of this Article, identification number plate affixing on all vehicles to be registered within the Country shall be made having Ethiopian map and given national identification sign "ETH", in addition, Geez "ኢት" and Latin words in accordance with international treaties ratified by Ethiopia.
4) The Ministry shall produce identification number plates having consecutive numbers and containing three Latin words and four numbers.

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport and Logistics

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ልዩ መግለጫ ያለው የተለየ የመለያ ቁጥር ሠሌዳ ለሚጠይቅ ሰው ሚኒስቴሩ እንደሁኔታው በልዩ ሁኔታ ሊሰጥ ይችላል፡፡
6) የሞተር ሳይክል መለያ ቁጥር ሠሌዳዎች ቁጥር አሰጣጡ በሦስት የላቲን ፊደላት እና ሦስት ቁጥሮች ሆኖ እንዲመረት ይደረጋል፡፡
7) ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ "ሀ" የተጠቀሱት የቀለም ኅብር እና የፊደል ጣምራዎች እንደተጠበቁ ሆነው ሚኒስቴሩ የመለያ ቁጥር ሠሌዳ ሲመረት ለቁጥጥር እና ለምዝገባ ዓላማ የሚያገለግሉ መረጃዎችን የሚሰጡ ምሥጢራዊ ምልክቶችን እያንዳንዱ የሠሌዳ ዓይነት የያዘ እንዲሆን ያደርጋል፡፡
8) ለቁጥጥር እና ለምዝገባ ዓላማ የሚያገለግሉ መረጃዎችን የሚሰጡ ምሥጢራዊ ምልክቶች ይዘት በሚኒስቴሩ ይወሰናሉ፡፡
9) ሚኒስቴሩ የተሽከርካሪዎችን የአገልግሎት ዓይነት መሠረት በማድረግ የታክሲ አገልግሎት የሚሰጡ፣ የንግድ አገልግሎት የሚሰጡ፣ የመንግሥት ተሽከርካሪዎች ቀለም ባለው ስቲከር እንዲለዩ ያደርጋል፡፡

5) Notwithstanding the provisions of sub-article (4) of this article, the Ministry may, under esceptinal circumstances, issue a separate identification nuber plate with a special description upon the request of an individual, as deemed appropriate in special case.
6) Identification number plates of motorcycle shall be manufactured by using three Latin words and three numbers.
7) Without prejudice to the colour combination and letter combination under Schedule "A" attached to this Directive, when the Ministry manufactures identification number plates shall make each number plate having security features giving information for the purpose of supervision and registration.
8) The Ministry shall determine the content of security features giving information for the purpose of supervision and registration.
9) The Ministry shall make vehicles giving taxi service, Commercial vehicles, public vehicles to affix sticker having colour on the basis of service type of vehicles.

10)ሚኒስቴሩ የተሽከርካሪ መለያ ቁጥር ሠሌዳ የሚታተምበት የቀለም ዓይነትን በተመለከተ ሁሉም ሠሌዳዎች መደባቸው ነጭ ሆኖ ፊደላቱ እና ቁጥሮቹ ጥቁር ቀለም እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

11)የዓለም አቀፍ እና የአህጉር አቀፍ ተቋማት፣ የኮር ዲፕሎማት እና የዕርዳታ ድርጅት ተሽከርካሪ መለያ ቁጥር ሠሌዳዎች መደባቸው ነጭ ሆኖ በሠሌዳው ላይ ልዩ ምልክት በማድረግ ጽሑፉ በጥቁር ቀለም ሆኖ እንዲታተሙ ይደረጋል፡፡

12)የሞተር ሳይክል የመለያ ቁጥር ሠሌዳ መደቡ ነጭ፣ ጽሑፉ በቀይ ቀለም ሆኖ እንዲታተም ይደረጋል፡፡

13)የልዩ ተንቀሳቃሽ ሠሌዳ መደባቸው ነጭ፣ ጽሑፉ በቀይ ቀለም ሆኖ “ልተመ” እና “SME” የሚል ምሕፃረ-ቃል ተጨምሮ እንዲታተም ይደረጋል፡፡

14)በኤሌክትሪክ ወይም በሌሎች ታዳሽ ኃይሎች የሚሠራ የተሽከርካሪ የመለያ ቁጥር ሠሌዳ መደቡ ነጭ ሁኖ ጽሑፉ አረንጓዴ ቀለም እንዲሆን ይደረጋል፡፡

15)የአካል ጉዳተኛ ተሽከርካሪ የመለያ ቁጥር ሠሌዳ ነጭ መደብ ከጥቁር ፊደላትና ቁጥሮች ጋር የያዘ ሆኖ፤ ከተሽከርካሪው አካል ላይ ከፊት እና ከኋላ የዊልቸር ምልክት፣“PD” የሚል

10) The Ministry shall manufacture all vehicles identification number plates to be ground in white, the words and the numbers in black colour.

11) Identification number plates of vehicles of international institutions, intercontinental institutions, Core Diplomats and Aid organizations shall be manufactured the plate ground in white and having special identification sign on it, and the writing in black colour.

12) Identification number plates of motorcycle shall be manufactured the ground in white and the writing in red colour.

13) Identification number plates of Special Mobile Equipment shall be manufactured the ground in white the writing in red colour and with abbreviation “ልተመ” and “SME” on it.

14) Identification number plates of Vehicle Used Electric or Other Renewable Energy shall be the ground in white and the writing in green colour.

15) Identification number plate of Vehicle of Handicap persons shall be the ground in white colour and the writing in black colour; and then,

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport and Logistics

የላቲን እና “አጉ” የሚል የግዕዝ ምሕፃረ-ቃላትን ይዞ መደቡ ነጭ፣ ጽሑፉ ጥቁር ቀለም የሆነ ስቲከር እንዲለጥፉ ይደረጋል፡፡

16) በሀገሪቱ ውስጥ ለሚገኙ ዓለም አቀፍ እና አህጉር አቀፍ ድርጅቶች፣ ኢምባሲዎች፣ ግብረ-ሠናይ ድርጅቶች የሚሰጥ የተሽከርካሪ መለያ ቁጥር ሠሌዳ ላይ የሚኖረው ልዩ ምልክት እና ቀለም ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ “ሀ”መሠረት ይሆናል፡፡

17) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የፖሊስ አካላት ተሽከርካሪዎች መለያ ቁጥር ሠሌዳን በሚመለከት ተቋማቱ በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት እንዲታተም ይደረጋል፡፡

18) በተሽከርካሪ ላይ የሚለጠፉ የአገልግሎት መለያ ስቲከር ዓይነቶች፣ ይዘት፣ ቅርፅ፣ ፊደላት እና ቁጥሮች ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ”ሀ” መሠረት ይሆናል፡፡

## 6. ስለ ተሽከርካሪ የመለያ ቁጥር ሠሌዳ አሰጣጥ

1) የተሽከርካሪ አስመጪነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የተሰጠው ድርጅት ተሽከርካሪውን ወደ ሀገር ውስጥ ካስገባ በኋላ ጥያቄ ሲያቀርብ ሚኒስቴሩ እንደሁኔታው በሚወስነው ቁጥር ልክ

shall affix sticker having wheel chair sign and containing abbreviations of Latin word "PD" and Geez “**አጉ**” in front and back of the vehicle.

16) Special sign and colour of identification number plates of vehicles of international institutions, intercontinental institutions; Embassies' and Charity organizations living within the country shall be in accordance with Schedule "A" attached to this Directive.

17) Notwithstandng the provisions of sub-article (1) of this Article, identification number plates of vehicles of Police organs shall be manufactured according to the request of their institutions.

18) Types, content, shape, words and numerals of Service type identification stickers affixing on vehicles shall be in accordance with the Schedule "A" attached to this Directive.

## 6. Service of vehicles identification number plate

1) Upon the importation of vehicle by an enterprise which has importing competency license, the ministry shall determine the number of transferable identification number plates to be

ለአስመጪው ተላላፊ የመለያ ቁጥር ሠሌዳ ይሰጠዋል፡፡

2) አምራች ወይም ገጣጣሚ ድርጅቶች ላመረቷቸው ወይም ለገጣጠሟቸው ተሽከርካሪዎች አስፈላጊ ሰነዶችን አሟልተው በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት ሚኒስቴሩ እንደ ሁኔታው በሚወስነው ቁጥር ልክ ለአምራቹ ወይም ለአስመጪው ተላላፊ የመለያ ቁጥር ሠሌዳ ይሰጣል፡፡

3) ማንኛውም ሰው የመለያ ቁጥር ሠሌዳ ሲጠፋ፣ሲበላሽ ወይም ቀለሙ ሲለቅ የተሽከርካሪ መለያ ቁጥር ሠሌዳ ምትክ ይሰጠዋል፡፡

4) ሚኒስቴሩ ለተሽከርካሪዎች የተሰጣቸውን መለያ ቁጥር ሠሌዳ መረጃ በሲስተም አደራጅቶ ይይዛል፣ አግባብነት ላላቸው አካላትም ይሰጣል፡፡

5) ለመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች የሚሰጠው ተጨማሪ የተሽከርካሪ መለያ ቁጥር ሠሌዳ ከሚመለከተው የደኅንነት ተቋም በሚጻፈው የፈቃድ ደብዳቤ መሠረት የሚሰጥ ይሆናል፡፡

6) የተሽከርካሪ መዝጋቢ አካላት የሚወገዱ የተሽከርካሪ መለያ ቁጥር ሠሌዳዎችን በአግባቡ ሰብስበው ያስወግዳሉ፡፡

7) ማንኛውም ሰው በወሰደው ተሽከርካሪ መለያ ቁጥር ሠሌዳ ተሽከርካሪውን በሚያስመዘግብበት ወቅት በሌሎች ሕጎች

issued, as deemed necessary based on circumstances.

2) Upon reciving a formal request from vehicle manufactures or assemblers for manufactured or assembled vehicles, the Ministry shall, based on the special circumstances, determine and issue the appropriate number of transferable identification number plates.

3) Any person shall be given replacement of vehicles identification number plate when the identification number plate disappeared, perished or fade out its colour.

4) The Ministry shall arrange and take information of identification number plate given to vehicles through system and give to appropriate organs.

5) Additional identification number plate to be given government officials shall be in accordance with the permission letter written from the concerned organ.

6) Registrar organs shall collect and discard vehicles identification number plates that to be discarded.

7) Any person who takes identification number plates and submits his vehicle

ከተቀመጡት መስፈርቶች በተጨማሪ በዚህ መመሪያ በተወሰነው መሠረት የአገልግሎት ዓይነቱን የሚገልጽ ስቲከር አሠርቶ መለጠፍ አለበት፡፡

## 7. የተሽከርካሪ አምራች፣ ገጣጣሚ፣ አስመጪ ድርጅት እና ግለሰቦች ግዴታዎች

የተሽከርካሪ አምራች ወይም ገጣጣሚ ወይም አስመጪ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች የሚከተሉት ግዴታዎች አሉባቸው፡-

1) ላመረቷቸው ወይም ለገጣጠሟቸው ወይም ላስመጧቸው ተሽከርካሪዎች የተሽከርካሪ ተላላፊ የመለያ ቁጥር ሠሌዳ እንዲሰጣቸው ዓይነትና ብዛቱን ጠቅሰው ለሚኒስቴሩ በጽሑፍ ጥያቄ የማቅረብ፤

2) ሚኒስቴሩ ወስኖ በሰጣቸው የተላላፊ የመለያ ቁጥር ሠሌዳ ብዛት ልክ ክፍያ የመፈጸም፤

3) ባመረቷቸው፣ በገጣጠሟቸው ወይም ባስመጧቸው እና ተሸጠው ባልተመዘገቡ ተሽከርካሪዎች ላይ የተላላፊ የመለያ ቁጥር ሠሌዳ እና የድርጅቱን ባለቤት ወይም ሕጋዊ ተወካይ ሙሉ አድራሻ የሚገልጽ ስቲከር የመለጠፍ፤

4) ተሽከርካሪ የገዟቸውን አካላት ለምዝገባ በሚልኩበት ጊዜ የለጠፉትን የተላላፊ መለያ ቁጥር ሠሌዳ ትክክለኛነት በማረጋገጥ አስፈላጊውን መረጃ

to the registry shall affix Sticker indicating type of service in accordance with this Directive in addition to requirements provided under other laws.

## 7. Obligations of Manufacturing, Assembling, Importing Enterprises or Individuals

Manufacturing, Assembling, Importing Enterprises or Individuals have the following obligations:

1) Submitting a formal writeen request to the Ministry, specifying the type and quantity of vehecles that have been manufactured, assembled, or imported, in oreder to obtain transferable identification number plates.

2) Paying fees proportional to the quantity of transferable identification number plates, as determined by the Ministry.

3) Affixing transferable identification number plates, along with a sticker that includes the full address of the enterprise owner or the legal agent, to all vehicles thata have no beeb sold.

4) When sending the buyers of vehicle to the registry, they shall assert accuracy of the transferable identification number plate tied on the vehicle with relevant

አሟልተው ለመዝጋቢ አካላት የመላክ፤

5) ከየትኛውም ተሽከርካሪ አምራች ወይም ገጣጣሚ ወይም አስመጪ ድርጅት ተሽከርካሪን የገዛ ሰው ከገዛበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ወደ መዝጋቢ አካላት ዘንድ ቀርቦ ማስመዝገብ አለበት፡፡

6) ከየትኛውም ተሽከርካሪ አምራች ወይም ገጣጣሚ ወይም አስመጪ ድርጅት ተሽከርካሪን የገዛ ሰው ከድርጅቱ የተሰጠውን የተሽከርካሪ ተላላፊ መለያ ቁጥር ሠሌዳ በመለጠፍ ተሽከርካሪውን ለማስመዝገብ ወደ መዝጋቢው አካል ሲንቀሳቀስ የተሽከርካሪውን መረጃ የያዘና የድርጅቱ ማኅተም ያረፈበት የመንቀሳቀሻ ቅጽ መያዝ አለበት፡፡

8. <u>የተሽከርካሪ መዝጋቢ አካላት ግዴታዎች</u>

የተሽከርካሪ መዝጋቢ አካላት የሚከተሉት ግዴታዎች አሉባቸው፡-

1) በሀገር ውስጥ ለሚመረቱ ወይም ለሚገጣጠሙ ወይም ከውጭ ሀገር ለሚገቡ ተሽከርካሪዎች የተሰጣቸውን የተሽከርካሪ ተላላፊ መለያ ቁጥር ሠሌዳ ለጥፈው ሲቀርቡ አስፈላጊ መረጃዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ የመመዝገብና ቋሚ የመለያ ቁጥር ሠሌዳ የመስጠት፤

2) ለሚመዘግቧቸው ተሽከርካሪዎች አስፈላጊውን የምዝገባ የአገልግሎት ክፍያ የማስከፈል፤

information.

5) A person who purchases a vehicle from any manufacturer, assembler or importer shall submit the vehicle to registrar within one month starting from the date of purchase.

6) A person who buys vehicle from any manufacturer or assembler or importer enterprise moves to registrar by tying transfrable identification number plate shall take a letter describing information of the vehicle attested by stamp of the enterprise whice allows him to move.

8. **<u>Obligations of vehicles registrars</u>**

Vehicles registrars have the following obligations:

1) To register manufactured or assembled locally or imported vehicles when they appeared by tying their transferable identification number plate given to them by asserting the fulfilment of necessary information and issue a permanent identification number plate.

2) To collect the necessary registration service fee for the vehicles registered by them.



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport and Logistics

3) የአገልግሎት ዓይነታቸውን ለመለየት እንዲያስችል የተዘጋጀውን ስቲከር በተሽከርካሪው በግራ እና በቀኝ በር ላይ እንዲለጠፍ የማድረግ፤

4) የሚለጠፉት ስቲከሮች ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ "ሀ" መሠረት መሆናቸውን የማረጋገጥ፤

5) የአገልግሎት ዓይነታቸውን ለሚቀይሩ ተሽከርካሪዎች የተሽከርካሪ መለያ ቁጥር ሠሌዳ ለውጥ ማድረግ ሳያስፈልግ የለጠፉትን ስቲከር ብቻ ወደ ሚቀይሩት የአገልግሎት ዓይነት በመቀየር የአገልግሎት ለውጡን ምዝገባ የማድረግ፤

6) የተመዘገቡትን ተሽከርካሪዎች በየአገልግሎት ዓይነታቸው በመለየት በሲስተም ወደ ሚኒስቴሩ የመረጃ ቋት የመላክ፤

7) የአገልግሎት ለውጥና ዝውውር ለሚያደርጉ ተሽከርካሪዎች ለአገልግሎት ዓይነት መለያ የተለጠፈላቸውን ስቲከር በማንሳት መሸኛ የመስጠት፤

8) የሚዘዋወሩ ተሽከርካሪዎችን የአገልግሎት ዓይነት መለያ ስቲከር ቀደም ሲል ለመዘገበው አካል እንዲመለስ በማድረግና መሸኛ ማቅረቡን በማረጋገጥ የተሽከርካሪዎችን ምዝገባ የማድረግ፤

3) To make affixing sticker prepared to indicate service type on the left and the right door of the vehicle.

4) To check the stickers to be affixed are in accordance with the schedule "A" attached to this Directive.

5) To make change of registry for vehicles changing service type without changing identification number plate only by changing the sticker affixed to the service type that will be changed.

6) To send using the system the registered vehicles to Central Data of the Ministry by separating in their service type.

7) To give passing letter to vehicles that making change of service type and transfer by getting off the sticker affixed to indicate their service type.

8) To ascertain submission of passing letter and register transferred vehicles by returning the given sticker indicating service type to the previous registrar.

9. **ለተሽከርካሪ አምራች ወይም ገጣጣሚ ወይም አስመጪ ድርጅት ወይም ግለሰብ ሠሌዳ ለማግኘት የሚያስፈልጉ ሰነዶች**

ማንኛውም የተሽከርካሪ አምራች ወይም ገጣጣሚ ወይም አስመጪ ድርጅት ወይም ግለሰብ የተሽከርካሪ መለያ ቁጥር ሠሌዳ ለማግኘት ከዚህ በታች የተመለከቱትን ሰነዶች ማሟላት ይጠበቅበታል፡-

1) የማመልከቻ ቅጽ ሞልቶ የማቅረብ፤
2) ያመረታቸውን ወይም የገጣጠማቸውን ወይም ያስመጣቸውን ተሽከርካሪዎች በመግለፅ እና የአገልግሎት ክፍያ የፊፀመበት ደረሰኝ ዋናውን እና የማይመለስ አንድ ፎቶ ኮፒ የማቅረብ፤
3) ተሽከርካሪ የገዛ ግለሰብ የጉምሩክ ዲካላራሲዮን እና የአገልግሎት ክፍያ የፊፀመበት ደረሰኝ ዋናውን እና የማይመለስ አንድ ፎቶ ኮፒ የማቅረብ፤
4) የታደሰ የብቃት ማረጋገጫ፣ የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት እና የፀና የንግድ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ዋናውን እና የማይመለስ አንድ ፎቶ ኮፒ የማቅረብ፤
5) አገልግሎቱን የሚጠይቀው ራሱ ባለቤቱ ከሆነ የታደሰ የነዋሪነት መታወቂያ ወይም የጸና ፓስፖርት ዋናውን እና የማይመለስ አንድ ፎቶ ኮፒ ወይም በውክልና ከሆነ የተወካይ የታደሰ

9. **Documents required to obtain plate for Vehicles Manufacturer, Assembler or Importer Enterprises or Individuals**

Any Vehicles Manufacturer, Assembler or Importer Enterprises or Individual shall fulfil the following documents to obtain vehicles identification number plate:

1) To fill and submit application form;
2) To submit the description of manufactured or assembled or imported vehicles accompanied by recipt of service fee original and copy not to be returned;
3) Individual who purchased a vehicle has to submit customs declaration accompanied by recipt of service fee original and copy not to be returned;
4) To submit renewed competency license, commercial registration certificate, valid business license certificate original and one copy not to be returned;
5) To submit identity card or valid passport original and one copy not to be returned where the request is by the owner or if the request is submitted by agent, identity card or original valid passport of the agent and one copy not to be

የነዋሪነት መታወቂያ ወይም የፀና ፓስፖርት እና በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ አገልግሎት የተረጋገጠ የውልክና ሥልጣን ማስረጃ ዋናውን እና የማይመለስ አንድ ፎቶ ኮፒ የማቅረብ፤

# ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 10.ክልከላዎች

ለማንኛውም የተሽከርካሪ አምራች ወይም ገጣጣሚ ወይም አስመጪ ድርጅት ወይም ግለሰብ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ተግባራት መፈፀም የተከለከለ ነው፡-

1) ከተሰጠውን የተላላፊ ወይም የቋሚ መለያ ቁጥር ሠሌዳ ውጭ የሌላ ድርጅትን ወይም ግለሰብን የመለያ ቁጥር ሠሌዳ መለጠፍ፤
2) ለተሽከርካሪው የተሰጠውን የመለያ ቁጥር ሠሌዳ ለሌላ ድርጅት ወይም ግለሰብ አሳልፎ መስጠት፤
3) ማንኛውም ሰው መለያ ቁጥር ሠሌዳ ያልለጠፈ ተሽከርካሪ ይዞ በማንኛውም ቦታ መንቀሳቀስ፤
4) ምዝገባ ሳያደርግ የመለያ ቁጥር ሠሌዳ የወሰደ ማንኛውም ሰው በተሽከርካሪ መለያ፣ መመርመሪያና መመዝገቢያ አዋጅ ቁጥር 681/2002 አንቀጽ 21 (2) ላይ ለተመለከቱት ዓላማዎች ካልሆነ

returned or if the request is by the agent, the original document of power of attorney authenticated by the Documents Authentication and Registration Service and one copy not to be returned;

# Part Tthree

## Miscellanies provisions

### 10.Prohibitions

Commission of the following acts is prohibited to any Vehicles Manufacturer, Assembler or Importer Enterprises or individual:

1) Affixing trasferable or permanent identification number plates on vehicle other than allowed identification number plates to the enterprise or individual;
2) Transferring to enterprise or individual other than the vehicle to which the identification number plates is issued;
3) Moving a vehicle to any place without affixing identification number plates issed to the vehicle;
4) Any person who take identification number plate to his vehicle but not yet registered shall not drive the vehicle for any purose other than described under Vehicle Identification, Inspection and

በስተቀር ተሽከርካሪውን ማንቀሳቀስ፤

5) ከየትኛውም ተሽከርካሪ አምራች ወይም ገጣጣሚ ወይም አስመጪ ድርጅት ተሽከርካሪን የገዛ ሰው ከሽያጭ ቦታ ወደ መዝገቢ አካል ለመንቀሳቀስ ከሚኒስቴሩ የመንቀሳቀሻ ፈቃድ አለመያዝ፤
6) ተሽከርካሪውን በሽያጭ በሚያስተላልፍበት ወቅት የተሳሳተ ወይም ሐሰተኛ የተሽከርካሪ መለያ ቁጥር ሠሌዳ ለጥፎ መገኘት፤
7) ይህ መመሪያ በሥራ ላይ ከዋለ በኋላ ቀደም ሲል የነበሩ የተላላፊ እና የዕለት የተሽከርካሪ መለያ ቁጥር ሠሌዳን በተሽከርካሪ ላይ ለጥፎ መንቀሳቀስ፤

## 11.<u>አስተዳደራዊ እርምጃዎች</u>

ማንኛውም ተሽከርካሪ አምራች ወይም ገጣጣሚ ወይም አስመጪ ድርጅት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 ስር ከተመለከቱት ክልከላዎች መካከል አንዱን ፈጽሞ ከተገኘ በወንጀል ሕግ መጠየቁ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1) ለመጀመሪያ ጊዜ ከሆነ የተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለአንድ ወር ታግዶ ተሽከርካሪዎቹም በዚሁ ጊዜ ውስጥ ምዝገባ እንዳያገኙ ይደረጋል፡፡
2) ጥፋቱን ለሁለተኛ ጊዜ ፈጽሞ ከተገኘ የተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ተሰርዞ፣ ተሰማርቶበት ከነበረው ሥራ ለሁለት ዓመታት ይታገዳል፡፡

Registration Proclamaton No.681/2010;

5) Moving to registrar without permission letter given by the Ministry when the person purchases a vehicle from any manufacturer, assembler or importer.
6) Affixing invalid or forged identification number plates during transfer of vehicle in sale;
7) Affixing previous transferable and temporary vehicles identification number plates and moving after the coming into force of this Directive.

## 11.<u>Administrative matures</u>

Any Vehicles Manufacturer, Assembler or Importer Enterprises commits one of the prohibitions provided under Article 10 of this Directive, without prejudice to the criminal law;

1) For the first time the competency license shall be suspended for one month and the vehicles shall not be registered within this period of time.
2) If the fault is for the second time, the given competency license shall be cancelled and suspended from the field ingeged in for two years.

3) ጥፋቱን ለሦስተኛ ጊዜ ፈጽሞ ከተገኘ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱ ተሰርዞ፣ ተሽከርካሪው ወይም ተሽከርካሪዎቹ ለስድስት ወር ምዝገባ እንዳያደርግ ይደረጋል፡፡

## 12.<u>የቅሬታ አቀራረብ እና አፈታት ሥነ ሥርዓት</u>

1) በዚህ መመሪያ መሠረት በተሰጠው አገልግሎት ቅሬታ ያለው ማንኛውም አካል ቅሬታውን ለሚኒስቴሩ የቅሬታ ማስተናገጃ ክፍል ቅሬታው በተፈጠረ በአሥር ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ማቅረብ ይችላል፡፡
2) የሚኒስቴሩ የቅሬታ ማስተናገጃ ክፍል ለቀረበው ቅሬታ በአምስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ለቅሬታ አቅራቢው በጽሑፍ ምላሽ መስጠት አለበት፡፡
3) የሚኒስቴሩ የቅሬታ ማስተናገጃ ክፍል በሰጠው ምላሽ ቅር የተሰኘ ሰው ምላሹ ከደረሰው ቀን ጀምሮ ባሉት አምስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን በጽሑፍ ለሚኒስትሩ ማቅረብ ይችላል፡፡
4) ሚኒስትሩ ለቀረበው ቅሬታ በአሥራ አምስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሰጣል።

3) If the fault is for the third time, the given competency license shall be cancelled and his vehicle or vehicles shall be prohibited from registration for six months.

## 12.<u>Complaint Review Procedure</u>

1) Any person who is dissatisfied with the service provided in accordance with this directive shall submit the complaint in writing to the complaint handling division of the Ministry within ten consecutive working days from the date of the complaint is occured.
2) The complaint handling division of the Ministry shall give response in writing to the complaint within five consecutive working days.
3) A person who is dissatisfied with the response of the complaint handling division of the Ministry shall submit the complaint in writing to the minister within five consecutive working days from the date of response is given.
4) The minister shall give final written administrative decision within fifteen consecutive working days.

5) ሚኒስትሩ በሚሰጠው የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ቅሬታውን ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

## 13.<u>የአገልግሎት ክፍያ</u>

1) ማንኛውም አካል በዚህ መመሪያ መሠረት የተሽከርካሪ መለያ ቁጥር ሠሌዳ ሲወስድ እና የተለያዩ አገልግሎቶችን ለማግኘት የአገልግሎት ክፍያ መክፈል አለበት፡፡
2) የተሽከርካሪ መለያ ቁጥር ሠሌዳ የአገልግሎት ክፍያ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

## 14.<u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>

ማንኛውም ሰው ይህ መመሪያ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ለተመዘገቡ ተሽከርካሪዎች ሚኒስቴሩ በሚያዘጋጀው የጊዜ ሠሌዳ መሠረት የቀድሞውን ሠሌዳ ለመዝጋቢው አካል በመመለስ አዲስ የተሽከርካሪ የመለያ ቁጥር ሠሌዳ መውሰድ አለበት፡፡

## 15.<u>ስለ መረጃ አያያዝ ሥርዓት</u>

ሚኒስቴሩ የመለያ ቁጥር ሠሌዳ አገልግሎት አሰጣጥን ለማስተግበር እና የተሽከርካሪዎችን መረጃ በአግባቡ ለመያዝ የሚያገለግል

5) Any person who is dissatisfied with the final administrative decision given by the Minister can submit his complaint to the appropriate court.

## 13.<u>Service fee</u>

1) Any person has to pay the prescribed service fee for labelling and taking vehicles identification number plates and to obtain other different services in accordance with this Directive.
2) The value of seles of vehicles of identification number plates and the service fee shall be determined by The Councile of Ministers.

## 14.<u>Transitory provisions</u>

Any person who has possession of the previous plate shall retun to the registrar, and takes new identification number plates for his vehicles registered prior to the enforcement of this Directive in accordance with the time schedule determined by the Ministry.

## 15.<u>Information holding System</u>

The Ministry shall develop Integrated Plate Registration System for proper application of identification number plate service and Vehicle registration.

የተቀናጀ የመለያ ቁጥር ሠሌዳ አመዘጋገብ ሥርዓት በማልማት ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

**16.<u>የተሻሩ ሕጎች</u>**

ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች አስመጪዎች የተላላፊ መለያ ቁጥር ሠሌዳ አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 681/2013 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

**17.<u>መመሪያውን ስለማሻሻል</u>**

ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማንኛውም ጊዜ መመሪያውን ማሻሻል ይችላል፡፡

**18.<u>መመሪያው ስለሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ድረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አለሙ ስሜ (ዶ/ር)**
**የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር**
**ሚኒስትር**

**16.<u>Repealed laws</u>**

Imports of used vehicles and utilization of transferable identification number plate directive No.681/2021 is repealed by this Directive.

**17.<u>Amendment of the Directive</u>**

The Ministry where it deems necessary may amend the Directive at any time.

**18.<u>Effective date of the Directive</u>**

This directive shall be effective from the date of its registration by the Ministry of Justice and its uploaded on the website of the Ministry of Transport and Logistics.

**Alemu Sime(Phd)**
**Minister of**
**The Ministry of Transport and**
**Logistics**

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport and Logistics

## አባሪ

## ሠንጠረዥ "ሀ":- የተሽከርካሪ መለያ ቁጥር ሠሌዳ ዓይነቶች እና ምልክቶች

| ተ.ቁ | የአገልግሎት ዓይነት | የቀለም ኅብር መለያ ቁጥር/የፊደላት ጥምርታ/ | | ትርጉም |
|---|---|---|---|---|
| | | ሠሌዳ | ስቲከር | |
| 1. | ታክሲ | ነጭ መደብ ከጥቁር ፊደላትና ቁጥሮች ጋር "ETH"፣ "ኢት" የተጻፈበት እና የኢትዮጵያ ካርታ ምልክት | ነጭ መደብ ከቀይ ፊደላትና ቁጥሮች ጋር የመለያ ቁጥር ሰሌዳው እና ታክሲ የሚል ጽሑፍ የተጻፈበት | በታክሲ አገልግሎት የተሰማሩ ተሽከርካሪዎች |
| 2. | የቤት | ነጭ መደብ ከጥቁር ፊደላትና ቁጥሮች ጋር "ETH"፣ "ኢት" የተጻፈበት እና የኢትዮጵያ ካርታ ምልክት | ስቲከር አይለጥፍም | ለግልና ለቤተሰብ አገልግሎት እንዲውል ለተመዘገበ ተሽከርካሪዎች የሚሰጥ |
| 3. | የንግድ | ነጭ መደብ ከጥቁር ፊደላትና ቁጥሮች ጋር "ETH"፣ "ኢት" የተጻፈበት እና የኢትዮጵያ ካርታ ምልክት | ነጭ መደብ አረንጓዴ ፊደላትና ቁጥሮች ጋር የመለያ ቁጥር ሰሌዳው የተጻፈበት | በንግድ የመንገድ ማመላለሻ ለተመዘገቡ ወይም ለሚከራዩ ተሽከርካሪዎች የሚሰጥ |
| 4. | የመንግሥት | ነጭ መደብ ከጥቁር ፊደላትና ቁጥሮች ጋር "ETH"፣ "ኢት" የተጻፈበት እና የኢትዮጵያ ካርታ ምልክት | የመንግሥት ተቋሙ ስም እና አርማ የተጻፈበት | ንብረትነታቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶች ለሆኑ ተሽከርካሪዎች የሚሰጥ |
| 5. | የሃይማኖት ተቋማት እና ማኅበራት | ነጭ መደብ ከጥቁር ፊደላትና ቁጥሮች ጋር "ETH"፣ "ኢት" የተጻፈበት እና የኢትዮጵያ ካርታ ምልክት እና 5 ቁጥር የተጻፈበት | ነጭ መደብ ብርትኳናማ ፊደላትና ቁጥሮች ጋር የማኅበሩ ስም እና አርማ የተጻፈበት | ንብረትነታቸው የሃይማኖት ተቋማት፣የቀይ መስቀል ማኅበር፣የንግድ ያልሆኑ ማኅበራትና ለመሳሰሉት ተቋማት ተሽከርካሪዎች የሚሰጥ |
| 6. | ዓለም-አቀፍና አህጉር-አቀፍ ተቋማት | ነጭ መደብ ከጥቁር ፊደላትና ቁጥሮች ጋር "ETH"፣ "ኢት" የተጻፈበት፣ የኢትዮጵያ ካርታ ምልክት እና የተቋሙ ስም ምሕፃረ-ቃል በአማርኛ እና በላቲን የተጻፈበት | የተቋሙ ስም እና አርማ የተጻፈበት | ንብረትነታቸው የዓለም-አቀፍ ተቋማት፣የአህጉር አቀፍ ተቋማት እና የዕርዳታ ድርጅት ለሆኑ ተሽከርካሪዎች የሚሰጥ |

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport and Logistics

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | የእርዳታ ሰጭ ድርጅቶች | ነጭ መደብ ከጥቁር ፊደላትና ቁጥሮች ጋር "ETH"፣ "ኢት" የተጻፈበት እና የኢትዮጵያ ካርታ ምልክት እና 35 ቁጥር፣ "ዕድ" "AO" የሚል የተጻፈበት | የተቋሙ ስም እና አርማ የተጻፈበት | ንብረትነታቸው የእርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ለሆኑ ተሽከርካሪዎች የሚሰጥ |
| | | ነጭ መደብ ከጥቁር ፊደላትና ቁጥሮች ጋር የተቋሙ ስም ምሕፃረ-ቃል "CD" በላቲን እና "ኮዲ" የሚል በአማርኛ የተጻፈበት | የተቋሙ ስም እና አርማ የተጻፈበት | በዓለም-አቀፍ ተቋማት፣ በአህጉር አቀፍ ተቋማት እና በዕርዳታ ድርጅቶች ውስጥ የዲፕሎማቲክ መብት ላላቸው ባለሥልጣኖች ተሽከርካሪዎች የሚሰጥ |
| | ኤምባሲዎች | ነጭ መደብ ከጥቁር ፊደላትና ቁጥሮች ጋር ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚሰጣቸውን ቁጥር የሚይዝ | | በኤምባሲዎች ስም ለተመዘገቡ ተሽከርካሪዎች የሚሰጥ |
| 7. | በኤሌክትሪክ ወይም በታዳሽ ኃይል የሚሠሩ ተሽከርካሪዎች | ነጭ መደብ ከጥቁር ፊደላትና ቁጥሮች ጋር "ETH"፣ "ኢት" የተጻፈበት እና የኢትዮጵያ ካርታ ምልክት | መደቡ በነጭ ሁኖ ጽሑፉ አረንጓዴ ቀለም የሆነ አረንጓዴ ትራንስ ፖርት (Green Transport) የሚል የተጻፈበት | ከነዳጅ ውጭ በሆነ ኃይል ለሚሰሩ ተሽከርካሪዎች የሚሰጥ |
| 8. | የአካል ጉዳተኛ | ነጭ መደብ ከጥቁር ፊደላትና ቁጥሮች ጋር "ETH"፣"ኢት" የተጻፈበት እና የኢትዮጵያ ካርታ ምልክት | የዊልቸር ምልክት እና "አጉ" "PD" የሚል የተጻፈበት | በአካል ጉዳተኞች ሥም የተመዘገቡ ተሽከርካሪዎች |
| 9. | ባለሞተር ብስክሌት | ነጭ መደብ ከቀይ ፊደላትና ቁጥሮች ጋር "ETH"፣ "ኢት" የተጻፈበት እና የኢትዮጵያ ካርታ ምልክት | | በሞተር ሳይክል አገልግሎት የተመዘገቡ |
| 10 | ልዩ ተንቀሳቃሽ መሣሪያዎች | ነጭ መደብ ከቀይ ፊደላትና ቁጥሮች ጋር "ETH"፣ "ኢት" እና የኢትዮጵያ ካርታ ምልክት እና "ልተመ" "SME" የሚል የተጻፈበት | | ለማንኛውም ልዩ ተንቀሳቃሽ መሣሪያ የሚሰጥ |
| 11 | የተሳቢ | ነጭ መደብ ከጥቁር ፊደላትና ቁጥሮች ጋር "ETH"፣ "ኢት" እና | ነጭ መደብ አረንጓዴ ፊደላትና ቁጥሮች ጋር | ለተሳቢ ተሽከርካሪዎች የተሰጠ መሆኑን ይገልፃል |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ተሳቢ የሚል የተጻፈበት እና የኢትዮጵያ ካርታ ምልክት | የመለያ ቁጥር ሠሌዳው የተጻፈበት | |
| 12 | የተላላፊ ሠሌዳ | ነጭ መደብ ከጥቁር ፊደላትና ቁጥሮች ጋር ሆኖ፣ በግራ ክንፍ በኩል "ተላላፊ"የሚል ጽሑፍ ያለበት | | ለተሽከርካሪ አስመጪ፣ አምራች ወይም ገጣጣሚ የሚሰጥ ሠሌዳ ነው |

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport and Logistics

# Annex

## Schadule “A”:-Types of identification number plates and symbols

| No | Types of Services | Colour Combination and plate number/letter Combination | | Meaning |
|---|---|---|---|---|
| | | plate | Sticker | |
| | **Taxi** | White ground with black letters and numerals and containing “ETH”, “ኢ.ት.” and symbol of Ethiopian map | White ground with red letters and numerals and written on it identification number plate and the term “Taxi” | To be given for Vehicles engaged in Taxi Transport |
| 10. | **Private** | White ground with black letters and numerals “ETH”, “ኢ.ት.” and symbol of Ethiopian map | Does not affix sticker | To be given for vehicles registered for the private and family purpose |
| 11. | **Commercial** | White ground with black letters and numerals and containing “ETH”, “ኢ.ት.”, symbol of Ethiopian map | White ground with green letters and numerals and written on it identification number plate | To be given for Vehicles engaged in commercial road transport or rent |
| 12. | **Governmental** | White ground with black letters and numerals and containing “ETH”, “ኢ.ት.” and symbol of Ethiopian map | written on it the name and Logo of the government institution | To be given for Vehicles owned by government institutions |
| 13. | **Religious and Civic Societies** | White ground with black letters and numerals and containing “ETH”, “ኢ.ት.”, symbol of Ethiopian map and number **5** | White ground with orange letters and numerals and written on the name and logo of the Association | To be given for Vehicles owned by religious institutions, Red Cross association and such associations |
| 14. | **International And Intergovernmental** | White ground with black letters and numerals and containing “ETH”, “ኢ.ት.”, symbol of fEthiopian map and the abbreviation of the name of institution in Latin and Amharic | written on it the name and logo of the institution | To be given for Vehicles owned by International or Intergovernmental Institutions and Aid Organizations |
| | **Aid Organizations** | White ground with black letters and numerals and containing “ETH”, “ኢ.ት.”, symbol of Ethiopian map, number **35**, “AO” and “ዕ.ድ” | written on it the name and logo of the institution | To be given for Vehicles owned by Aid Organizations |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | White ground with black letters and numerals and written on it the abbreviation name of institution and in Latin "CD" and in Amharic "ኮዲ" | written on it the name and logo of the institution | To be given for Vehicles used by personnel with diplomatic status within International or Intergovernmental Institutions and Aid Organizations |
| | **Embassies** | White ground with black letters and numerals and the number given by Ministry of Foreign affairs | | To be given for Vehicles registered in the name of Embassies |
| 15. | **Vehicles used Electric or Renewable energy** | White ground with black letters and numerals and containing "ETH", "ኢ.ት" and symbol of Ethiopian map | Green ground, writing with white colour and written on it the term "Green Transport | To be given for Vehicles used out of fuel energy |
| 16. | **Vehicle of Handicap persons** | White ground with black letters and numerals and containing "ETH" "ኢ.ት" and symbol of Ethiopian map | Having the sign of wheel chair and written on it "አጉ" and "PD" | To be given for Vehicles in the name of physical disabled persons |
| 17. | **Motorcycle** | White ground with red letters and numerals and containing "ETH", "ኢ.ት" and symbol of Ethiopian map | | To be given for motorcycle |
| 10 | **Special Mobile Equipment** | White ground with red letters and numerals and containing "ETH", "ኢ.ት" , symbol of Ethiopian map,"SME" and "ልተመ" | | To be given for any Special Mobile Equipment |
| 11 | **Trailer** | White ground with red letters and numerals and containing "ETH", "ኢ.ት" , symbol of Ethiopian map ,"Trailer" and "ተሳቢ" | White ground with green letters and numerals and written on it identification number plate | To be given for any Trailer |
| 12 | **Transferable Plate** | White ground with black letters and numerals with legned **"ተላላፊ"** on the left hand side | | To be given for any importer, manufacturer and assembler |

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport and Logistics